
ADV1

አዲስ የልማት ራዕይ
አዲስ ቪዥን ለርኒንግ ማቴሪያልስ ማኑፋክቸሪንግ

Addis Development Vision

# የቋንቋ ትምህርት






አዲስ አበባ
ጥር 2003 ዓ.ም መጀመሪያ ታተመ
መስከረም 2009 ዓ.ም እንደገና ታተመ

..ማወቅ የሚገባዎት ትልቅ ቁም ነገር!

Addis Development Vision

አዲስ ዴቨሎፕመንት ቪዥን/ አዲስ ቪዥን ለርንኒግ ማቴሪያልስ ማኑፋክቸሪንግ በሙያ ስልጠና ማዕከሉ ዉስጥ የህፃናት ትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በማምረት ለኢንተርናሽናል፤ ለመንግስታዊና ለግል መዋዕለ ሕፃናት ድርጅት የትምህርት መርጃ መሳሪያ ገዢዎችን ጥያቄ በማስተናገድ ላይ ይገኛል፡፡



የወቅቱን የሕፃናትና ልጆች እዉቀት ለማስጨበጥ ያስችላሉ የተባሉትን ማስተማሪያ አዲስ ዘይቤ ያካተተ መሆኑ አስተማማኝ ያደርገዋል፡፡



ምርታችን ጥራት አስተማማኝና ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን የጠበቀ ሲሆን በትምርትና በሞያ ስልጠና የተሰማሩ ባለሙያዎች የረጅም ጊዜ ልምድ ዉጤት ነዉ፡፡



መርጃ መሣሪያዎቹ የዘመናዊ ትምህርት አሰጣጥ ስልትን ያገናዘቡ በመሆናቸዉ ለመዋዕለ ሕፃናትና ዕድሜያቸዉ እስከ 10 ዓመት ለሆናቸዉ ታዳጊ ልጆች ማስተማሪያነት ማገልገል ያስችላል፡፡

በተጨማሪም ድርጅታችን በትምህርት መርጃ መሳሪያዎች አጠቃቀምና ለመዋዕለ ሕፃናት መምህርነት ስልጠናዎችን ይሰጣል፡፡

ከ1990 ዓ/ም ጀምሮ በርካታ ት/ቤቶች ተጠቅመዉ በዉጤቱ ሲረኩበት በምርታችን እንኮራበታለን፡፡ እናንተም ተጠቀሙበት ዉጤታማነታችሁን ያሳድጋል፡፡

ISBN 978-99944-861-0-6

Printing by:- Star Printing Press

# መግቢያ

ሕፃናት በተፈጥሯቸው አንድ ነገር ላይ ትኩረት ሰጥተው ረዘም ላለ ጊዜ የመቆየት ትእግሥት አይኖራቸውም። በአንድ ሥፍራ ተቀምጠው ለሰዓት መቆየት ለሕፃናቱ በጣም አስቸጋሪ ነው። ለምሳሌ ለሕፃናት ተረት ወይም ታሪክ እየተነገራቸው እያለ ታሪኩ ወይም ተረቱ ትንሽ ረዘም ያለ ከሆነ ሕፃናቱ ይቁነጠነጣሉ። እርስ በርስ ማውራት ይጀምራሉ። ነገር ግን ሕፃናት በነፃነት እንዲንቀሳቀሱ ፈቅደንላቸው የሚሠሩትን ሥራ ብንመለከት በአንድ ነገር ላይ ትኩረት ሰጥተው ከማከናወን ይልቅ የሚያዩትን ነገር ሁሉ መነካካትና መሞከርን ይፈልጋሉ። የዚህ ዓይነቱ እንቅስቃሴ ደግሞ ሕፃናቱን የበለጠ እንዲሳተፉ ፍላጎት እንዲያድርባቸውና የተፈለገውን ግብ እንዲመቱ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደርጋል።

ሕፃናት እየሰሩ ወይም እየተጫወቱ ሲማሩና በቃል ሲማሩ የሚታየው ውጤት የተራራቀ እንደሆነ ስለ ህፃናት የትምህርት አቀባበል ያጠኑ ባለሙያዎች ያስረዳሉ። ከላይ የተጠቀሰውን የበለጠ ለመግለፅ **ሕፃን የሰማውን ይረሳል፣ ያየውን ያስታውሳል፣ የተገበረውን ያውቃል ይላሉ**። ስለዚህ ዘመናዊ ትምህርት አሰጣጥ ዘዴ በቃል ከሚሰጥ ትምህርት ይልቅ በተግባር እየሠሩ እንዲማሩ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥ በመሆኑ ሕፃናቱ የተሻለ እውቀት ጨብጠው እንዲወጡ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል። ህፃናት ራሳቸው ያከናወኑትን ክንዋኔ ወይም ግኝት መምህራን ከሚነግሯቸውና በቃል ከሚያስተምሯቸው በተሻለና በበለጠ ያስታውሳሉ። ለምሳሌ ከድንጋይ ይልቅ መስታወት በእጅ ሲነኩት ይለሰልሳል ብሎ ከመንገር ይልቅ በጥያቄ መልክ የትኛው ይለሰልሳል ሞክሩና ተናገሩ ቢባሉ ራሳቸው ሞክረው መልሱን ስለሚያገኙ አይረሱትም።

የአፀደ ሕፃናት ትምህርት ዓላማ ለሕፃናት ስብዕናና እድገት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት አካላቸው፣ ስሜታቸውንና ማህበራዊ ኑሯቸውን በተመለከተ ተገቢውን ዕውቀት ለመጨበጥ መሠረት መጣል ነው። ይህ መሠረት የሚጣለው ደግሞ ልዩ ልዩ ትምህርታዊ ክንዋኔዎችን ሥርዓት ባለው መንገድ፣ በቅደም ተከተልና መልክ-ብያዝ ሁኔታ ሲያከናወኑ እንደሆነ እሙን ነው። በመሆኑም አዲሱ ትውልድ ተመራማሪ፣ አምራችና በራሱ የሚተማመን ብቁ ዜጋ ሆኖ እንዲያድግ አቅጣጫ በመቀየስ በኩል ይህ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ይኖረዋል።

የሰው ልጅ በተከፋፈለ የእድገት ዘመን ውስጥ ሲታይ የመጀመሪያው የሕፃንነት ዘመኑ ፈጣን የአእምሮ እድገት የሚታይበት ወቅት ነው። ሕፃናት እያንዳንዳቸው የራሳቸው የሆነ የእድገት ፍጥነት አላቸው። ይሁን እንጂ የሁሉም ሕፃናት የአካል፣ የአእምሮ፣ የማስተዋልና የማገናዘብ ዕድገትና ብቃታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍ እያለ እንደሚሄድ ግልፅ ነው። ብዙ ጥናቶች እንደሚያረጋግጡት ለአንድ ሕፃን የዕድገት ፍጥነት ከፍተኛነትና ዝቅተኛነት ወሳኝ ከሆኑት መሠረታዊ ነገሮች አንዱ የረዳቶቻቸው ወይም የመምህራኖቻቸው ብቃት ነው። ስለዚህ የእነዚህ መምህራን እውቀት ከጊዜ ወደ ጊዜ በተለያዩ ዕውቀት ማዳበሪያ ተሀድሶዎች፣ አጫጭር ስልጠናዎችና ሴሚናሮች ማደግና መጎልበት ተገቢ ነው።

የቅድመ ሕፃናት ትምህርት መርሃግብር ተሳታፊ ሕፃናት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዋና ዋና ጥቅሞች ተጠቃሚዎች ናቸው።

ሀ. በጥራትና በወቅቱ (በዕድሜአቸው) ትምህርት የማግኘት ዕድል ይኖራቸዋል።

ለ. ከክፍል ወደ ክፍል ሳይዛወሩ ቀርተው የሚደግሙትንና ከት/ቤት አቋርጠው የሚወጡትን ተማሪዎች ቁጥር ይቀንሳል።

ሐ. በትምህርታቸው ብቁና ተወዳዳሪ ይሆናሉ።

መ. ማህበረሰባዊና ውስጣዊ ዕድገትን ያዳብራል

ሠ. በሕፃኑና በቤተሰቡ መካከል ያለውን ግንኙነት ያሳድጋል ፡፡

ረ. የሴቶችን የተሳትፎ ደረጃ (በተለይ የእናቶችን) ከፍ ያደርጋል፡፡

የሕፃኑ የአእምሮ እድገት ለወደፊት ሕይወቱ በጣም ወሳኝ በመሆኑ፣ ለወደፊቱ የአእምሮ ጤንነት፣ የመማርና የማደግ፣ (የባሕሪ ለውጥ) እጅግ መታሰብ ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ወቅት በጥንቃቄና በብቃት የተያዘ ሕፃን በት/ቤት ውስጥ በውጤቱ አመርቂ፣ ክህሎቱን በተሻለ ሁኔታ የሚያሳድግ፣ እንዲሁም በማህበረሳባዊና በኢኮኖሚ እድገቱ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንደሚያደርግ የተረጋገጠ ነው፡፡

የአፀደ ሕፃናት ዕድገት መርሃግብር መምህራን ለሕፃናቱ እንደ ወላጅ (እናት) እንደ ተንከባካቢና መሪ በመሆን ያገለግላሉ፡፡ ከላይ የተገለፁትን እጅግ ጠቃሚና ወሳኝ ውጤቶችን ለማግኘት ሕፃናት በራሳቸው ያለማንም ጣልቃ ገብነት (የረዳቶቻቸው እርዳታ ግን አይለያቸውም) በየቀኑ ለሰዓት በተመስጦ የሚሰሩት ተግባራዊ ስራ ለሕፃናቱ

- በነፃነት ያለምንም ፍርሃት አስፈላጊውን ስራ እንዲሰሩ ያደፋፍራል፡፡
- እራስን መምራት ያስተምራቸዋል፡፡
- ከሕይወት ጋር ያላምዳቸዋል፡፡
- ያላቸውን ግዴታ እንዲወጡ ያደርጋቸዋል፡፡
- የሰውነት  እንቅስቃሴያቸውን ያዳብራል፡፡

ወላጅና የሕፃናቱ መምሕራን ለዚህ ውጤት መምጣት ከፍተኛ ሚና መጫወት ይኖርባቸዋል፡፡ ለምሳሌ ሕፃናት የሚያድጉበትን አካባቢ በጥሩ ሁኔታ ማመቻቸትና ሕፃናቱ የሚሠሩትን ሥራ ማዘጋጀት፣ በሚሠሩበት ወቅት በቅርብ ዕርዳታ መስጠትና ማበረታታት የመሣሠሉት ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡ አዋቂዎች የልጆቻቸውን ማንነት ለመፍጠር ያላቸው ሚና ቀላል ባይሆንም ሙሉ በሙሉ የወላጆች አስተዋፅኦ ለማለት ያስቸግራል፡፡ ማንነታቸውን ሊገነቡ የቻሉት  ልጆቹ በራሳቸው ሙከራና ጥረት ሲሆን ውጤቱ ያማረ ይሆናል፡፡ ሕፃናት ዕውቀትን በራሳቸው ወደ ራሳቸው ያመጣሉ፡፡ ይህን ያመጡትን እውቀት ከአእምሯቸው ሳይጠፋ በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ አብሯቸው ይኖራል፡፡ የስነ ልቦና አዋቂዎች እንደሚሉት አንድ ሕፃን ዕውቀትን መጣጭ አእምሮ የሚኖረው ከተወለደ እስከ 6 ዓመት ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህን ሕፃናት መንከባከብና በብቃት ማዘጋጀት ይኖርብናል፡፡ ለሕፃናት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ሕፃናት በራሳቸው ሠርተው እንዲማሩ የሚረዳ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴን መከተል እጅግ በጣም ጠቃሚ እንደሆነ በጥናት ተረጋግጧል፡፡

በዚህ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ የህፃናትን ፍላጎት ለማሟላት ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ከልደት እስከ 2½ ዓመት፣ ከ2½ ዓመት እስከ 6½ አመትና ከ6½ አመት እስከ 12 ዓመት በሦስት ደረጃዎች በመከፋፈል ይመለከታል፡፡ ሕፃናት የሚማሩት በእንቅስቃሴ (በመመራመር) በመስራት፣ ቅደም ተከተል በመጠበቅ፣ በመደጋገም፣ በምናብና በረቂቅ በግንኙነት እንደሆነ ያስረዳል፡፡ ህፃናት የመጀመሪያዎቹን ሁለቱ የዕድሜ ደረጃዎችን የስሜት ሕዋሳቶቻቸውን ማለት መንካት ማየት፣ መስማት፣ ማሽተትና መቅመስን በመጠቀምና ቁሳቁሶችን በመፍታትና በመግጠም መፍትሄ በመሻት ሲማሩ ከ6 ዓመት እስከ 12 ዓመት ያሉት ግን ረቂቅ የሆኑትን አዲስ በዳበረው ምክንያታዊነት፣ ግምታዊነት እንቅስቃሴ በመምርከዝ ዕውቀታቸውን ያዳብራሉ፡፡ እነዚህን ሕፃናት ለመርዳት ተስማሚና አመቺ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች ያስፈልጋሉ፡፡ መምህራን ዘዴውንና አጠቃቀሙን ካሳዩ በኋላ ሕፃናቱ ራሳቸው በነፃነት

የትምህርቱን ርዕስ እንዲመርጡ ይበረታታሉ። የትምህርት መርጃ መሳሪያዎቹ ከዚህ እንደሚከተሉት አምስት ዋና ክፍሎች ይኖሩታል።

I. የተግባራዊ እንቅስቃሴ መርጃ መሳሪያዎች
II. የስሜት እንቅስቃሴ መርጃ መሳሪያዎች
III. የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች
IV. የሒሳብ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች
V. የሳይንስ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች


## የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

የሕፃናት ቋንቋ እድገት በብዙ ጥናቶች እንደተጠቆመው ሕፃኑ ተወልዶ እስከ ስድስት አመት እድሜ ያለው ጊዜ ለቋንቋ እድገት የመሰረት መጣያው ዘመን መሆኑን ነው። በዚህ የእድሜ ክልል ሕፃናት የተለያዩ የድምፅ ምንጮችና የድምፅ ድግግሞሽን፣ መሰረታዊ ቃላትን የመረዳት እንዲሁም ለመናገር የመሞከሪያ ጊዜያቸው ነው። አፋችውን የሚፈቱትም በአካባቢያቸው ቋንቋ ሲሆን በዚህ ደረጃ ከመድረሳቸው በፊትም የራሳቸው የእድገት ደረጃ ስላላቸው ያንንም ማለፍ ግድ ይሆናል።

በጥቅሉ ስንመለከት እስከ ሶስትና አራት አመት የዕድሜ ክልል የሕፃናት የቃላት ክምችት እየሰፋ ቢሄድም ቃላትን ሁሉ በንግግር የመግለጽ ችሎታቸው የዳበረ አይደለም። ቢናገሩም አብዛኛውን ጊዜ በቃላት የተወሰነ ነው። በአረፍተ ነገር ቢናገሩም የኩልትፍና ባህርይ ስለሚታይባቸው በቋንቋ በኩል የሚታዩትን ስሕተቶች ለይቶ ማውጣት አስቸጋሪ ይሆናል። ከሶስትና ከአራት አመት በኋላ የቋንቋ እድገታቸውን በሚገባ ለመከታተልና በወቅቱ ሊደረግ የሚገባውን እንክብካቤ ለማድረግ እንችል ዘንድ የቋንቋ ትምህርት ዓላማን በመንደፍ፣ በእቅድና በመርሃ ግብር በመመራት እቅዱ ተግባራዊ የሚሆንበትን ዘዴ በመሻት ማስተማር ጥሩ ውጤት ያስገኛል። ስለዚህ ከዚህ በታች የሚቀርበው በአላማ ላይ የተመሰረተው የትምህርት መርጃና አቀራረብ የሕፃናትን የቋንቋ እድገት ያፋጥናል ተብሎ ይታመናል።

### 1. <u>የተከፋፈሉ የስዕል ዓይነቶች</u>

<u>መርጃ መሳሪያ</u>፡ -



- የተለያዩ የስዕል ካርዶች ሲሆኑ ከሕፃኑ አካባቢ ጋር የተያያዙ መሆን አለባቸው
- የቤት ዕቃዎችን የሚያሳዩ ስዕል ካርዶች
- የቤት እንስሳትን የሚያሳዩ የስዕል ካርዶች
- የዱር እንስሳትን የሚያሳዩ የስዕል ካርዶች
- የጓሮ አትክልቶችን የሚያሳዩ የስዕል ካርዶች
- የፍራፍሬ ዓይነቶችን የሚያሳዩ የስዕል ካርዶች
- የህንፃ መሳሪያዎችን የሚያሳዩ የስዕል ካርዶች
- የአበባ አይነቶችን የሚያሳዩ የስዕል ካርዶች

<u>ቀጥተኛ ዓላማ</u>

- ቃላትን ለማዳበር
- የሕፃናቱን የአካባቢ ግንዛቤ ለማዳበር
- አንድን ነገር ለመግለስ በራስ የመተማመንን ብቃት ለማጎልበት

አቀራረብ፡ -

- አንድ ነገር ለማቅረብ ጠረጴዛ ወይም ምንጣፍን መጠቀም
- የሚቀርበውን ነገር ለሕፃናቱ መንገር
- ሕፃናቱ ሳጥኑን ጠረጴዛ ላይ እንዲያስቀምጡ ጋብዟቸው
- ሁሉንም ስዕሎች ሕፃናቱ ለይተው እንዲያውቁ አሳዩዋቸው

- ስለ ስዕሉ ከሕፃናቱ ጋር ተወያዩ
- ስዕሎቹን አንድ በአንድ በማውጣት ሕፃናቱ እንዲወያዩበት እርዷቸው
- ያላወቁትን ስዕል ወደ ጎን አስቀምጡት
- ከዚያ የማያውቁትን ስም በሦስት ክፍለ ጊዜ አስተምሯቸው
- ልጆቹ የቁሶቹን ስሞች ካወቁ በኋላ በረድፍ ጠረጴዛ ላይ እንዲደረድሩት እርዱዋቸው
- ልጆቹ የማያውቁትን ስሞች አስተምሯቸው ወይም እያወቁ መናገር ያቃታቸውን ወይም እየተከላተፉ የሚናገሩት አስተካክለው እንዲናገሩ እርዷቸው
- ስማቸውን በሦስት ክፍለ ጊዜ ከዚህ በታች ባለው መንገድ አስተምሯቸው
  - አንዱን ስዕል በማምጣት ስሙን ንገሩና ፊታቸው አስቀምጡ
  - ሕፃናቱ ስዕሉን እንዲሰጧችሁ ወይም እንዲያሳዩአችሁ ጠይቁ
  - ሦስቱን ስዕል ብቻ እርዷቸው። ሕፃኑ ስዕሎቹን ይደባልቁ። ይህ ምንድነው ተብለው ሲጠየቁ ሕፃናቱም የቁሱን ስም ይናገራሉ።

*<u>መልመጃ 1</u>*

- ልክ ከላይ እንዳየነው ሕፃናቱ በሁሉም ስብስቦች ይሠራሉ
- ሕፃናቱ ከሌሎች ሕፃናት ጋር ስለ ስዕሉ ያዩትን ነገሮች በመወያየት ይሠራሉ

**<u>መልመጃ ሁለት</u>: -**

- ሕፃናቱ ከሳጥኑ ጋር ከተለማመዱ በኋላ ሁለቱን ሳጥኖች ይደባልቋቸዉ። ከዚያ ደግሞ በየቦታቸው ለይተው ያስቀምጧቸው

**<u>ዕድሜ</u>:** - 4½ እና ከዛ በላይ

በአብዛኛው ሕፃናት እንደ ባህሉ ሁኔታ የሚለምዱአቸው ቃላቶች የተወሰኑ ልዩነቶች ይኖራቸዋል። ለምሳሌ፡ - ፍራፍሬ፣ መሬትና ውሃ፣ የአትክልት አይነት፣ የወፎች አይነት ወዘተ..

## ፪. <u>ታሪክ መንገር</u>

**<u>አቀራረብ</u>: -**

- ሕፃናቱ ግማሽ ክብ ሰርተው እንዲቀመጡ ጋብዟቸው
- ትልቁ ልጅ ከኋላ ትንሹ ደግሞ ከፊት እንዲቀመጡ እርዷቸው
- የሁሉንም ሕፃናት ፊት ማየት መቻል አለባችሁ
- በሕፃናቱ የዕድገት ደረጃ የተመጠነ በቀላሉ ሊገባቸው የሚችለውን ታሪክ መምረጥ
- ታሪኩ ውስብስብ መሆን የለበትም
- አስፈሪ ታሪክ መሆን የለበትም
- መጨረሻው አስደሳች ታሪክ መሆን አለበት
- ታሪኩ አስተማሪ መሆን አለበት
- ታሪኩን ስትናገሩ ሕፃናቱን እያያችሁ መሆን አለበት

- ታሪኩን በሚስብ መንገድ መናገር ይኖርባችኋል ማለት የፊት እንቅስቃሴያችሁ የድምፃችሁን ከፍና ዝቅ በማድረግ ከታሪኩ ጋር አብሮ መሄድ አለበት
- በጣምም ማጋነን አስፈላጊ አይደለም
- እውነተኛና የሚስብ አድርጋችሁ ማቅረብ አለባችሁ
- ታሪኩን ከመጽሐፍ የምታነቡ ከሆነ፣ መጀመሪያ በደንብ መዘጋጀት አለባችሁ፡፡ ምክንያቱም እንዲስብ አድርጋችሁ ለማንበብና ልጆቹንም ቀና ብላችሁ ማየት ያስችላችኋል፡፡
- መጽሐፉ ስዕል ካለው ለልጆቹ አሳዩዋቸው፣ ይህም ታሪኩን ለመከታተል ይረዳቸዋል፡፡

**ዕድሜ፡-** 4½ አመትና ከዚያ በላይ

## 3. <u>የዜና ክፍለ ጊዜ</u>

<u>ቀጥተኛ ዓላማ፡-</u>

- ሕፃናት ሃሳባቸውን በቃላት እንዲገልፁ መርዳት

<u>አቀራረብ</u>

- የተወሰኑ ተማሪዎች አንድ ላይ በመሆን ዜናዎችን ይለዋወጣሉ
- ሕፃናቱ ዜናዎችን በድንገት ያቀርባሉ
- አስፈላጊ ሲሆን እረዳቶቻቸው ሕፃናቱ በመነሳት እንዲናገሩ ያበረታቷቸዋል
- ለሕፃናቱ በጓደኞቻቸው ፊት ቆመው መናገር መቻል በጣም ጠቃሚ ነው
- በራስ መተማመንንና ጥሩ ሃሳብ ማቅረብን ይለምዳሉ
- እረዳቶቻቸው የተፈለገውን ግብ ለመምታት የሚከተሉትን ክህሎት ማግኘት አለባቸው ፡
  1. እንዴት ሕፃናትን ማስጀመር እንደሚቻል
  2. የሕፃናትን ፍላጎት ማወቅ
  3. እንዴት ማበረታታት እንደሚቻል
  4. አንዳንድ ሕፃናት እጃቸውን ቢያነሱም ነገር ግን እረዳቶቻቸው ካላበረታቷቸው መናገር ስለማይችሉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው
  5. በመጀመሪያ ልጆቹ ይቀመጣሉ፡፡ ነገር ግን ወዲያው ሕፃናቱ ለመናገር ሲዘጋጁ እረዳታቸው ታበረታታቸዋለች
  6. በአንድ ርዕስ ተወስነው እንዲናገሩ መርዳት
  7. አንዳንድ ሕፃናት ለመጨረስ እርዳታ ይፈልጋሉ
  8. እረዳቶቻቸው እንዲጨርሱ ሊረዷቸው ይችላሉ

ለም<u>ሳሌ</u>፡- "ስለተናገርከው ታሪክ በጣም እናመሰግንሃለን" በማለት

- አንዱ ሌላውን እንዲያዳምጥ ማበረታታት
- በሕፃናቱም ሆነ በረዳታቸው የሚደረገውን ማቋረጥ መቆም አለበት
- ሕፃናቱ ሌላው ተናግሮ እስኪጨርስ ድረስ ተራቸውን መጠበቅ አለባቸው
- በሥነ ሥርዓት እንዲናገሩ መርዳት

- ክፍለ ጊዜው ሲያበቃ ቡድኑ፣ ንቁ ፍላጎት ያለውና ዝግጁ ይሆናል
- እንቅስቃሴው በዚህ ዓይነት ከቀጠለ በራስ መተማመናቸው የበለጠ ከፍ ይላል

## 4. ጥያቄያዊ ጨዋታ

**ቀጥተኛ ዓላማ፡-**

- የሕፃናቱን ሀሳብ ቅደም ተከተል ለማዳበር
- ራሳቸውን ሲገልፁ በአንድ በተወሰነ ርዕስ ላይ እንዲናገሩ ለመርዳት

**ኢ-ቀጥተኛ አላማ፡-**

- ታሪክ ለመፃፍ ዝግጁ ይሆናሉ፡፡

**አቀራረብ፡-**

- ቡዱኑ ውስጥ አራት ወይም ስድስት ሕፃናትን በማቀፍ የጥያቄ ጨዋታዎችን ማካሄድ ይቻላል
- ሕፃናቱ እንዲነጋገሩበት ርዕስ መምረጥ፣ ለምሳሌ፡- በዚያው ጊዜ የተፈፀመ ድርጊት ወይም የራሳቸውን ልምድ
- አረፍተ ነገሩ ባለቤት፣ ተሳቢና ግስን መያዝ አለበት
- በረዳታቸው የሚጠይቀው ጥያቄ እዚያው የሚመለስ መሆን አለበት
- ሕፃናቱም ጥያቄውን እንዲመልሱ ማበረታታት
- አንዱን መልስ ማስፋፋት፣ ሕፃናቱ የሰጡትን መልሶች ከዚህ ቀጥሎ ባለው ቀደም ተከተል መሰረት ማብራራት ፡-
    - በግሥ ዙሪያ ያለ ጥያቄ
    - በባለቤት ዙሪያ ያለ ጥያቄ
    - በተሳቢ ዙሪያ ያለ ጥያቄ
    - ድርጊትን የሚያሳዩ ግሶች በጣም የተሻሉ ናቸው

**ለምሳሌ፡** - ጠረገ፣ ዘመረ፣ ደረሰ ወዘተ

- ሰብለ ቤቷ አበባውን ውሃ አጠጣች
- ሰብለ ምን ስራች?
- ሰብለ ቤቷ አበባውን ውሃ አጣጣች፡፡
    - ስብለ ማን ናት?
    - ስብለ ቤቷ አበባውን ውሃ ያጠጣች ልጃገረድ ናት፡፡
    - ሰብለ የትኛውን አበባ ነው ውሃ ያጠጣችው?
    - ሰብለ ቤቷ ያለውን አበባ ውሃ አጠጣች፡፡

**ዕድሜ፡** - 4½ እና በላይ

- ጥያቄያዊ ጨዋታዎችን ከርዕሱ ጋር አያይዛችሁ ስታዘጋጁ የሚከተሉት ነጥቦች ማስታወስ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡
    - ሕፃናቱ ባዘጋጁት ወይም ባስተባበሩት ነገሮች ላይ የተመሰረተ ርዕስ መሆን የለበትም
    - የሚዘጋጀው ርዕስ በሕፃኑ ሚስጢራዊ በሆኑ ነገሮች ወይም በጣም ረጅም ጊዜ በቆየ ታሪክ ላይ የተመሠረተ መሆን የለበትም፡፡

## 5. የድምፅ ጨዋታታ

*መርጃ መሳሪያ፡-*

- በመማሪያ ክፍል አካባቢ ወይም በአትክልት ቦታ ያሉ ቁሶችና እቃዎች
- እያንዳንዱ ዕቃዎች የተለያዩ ድምፆችን የሚሰጡ መሆን አለባቸው

*ለምሳሌ*

- እንጨት፣ ቆርቆሮ፣ ማንኪያ ወዘተ
- ለሕፃናቱ አዲስ ያልሆነ ቁስ ምረጡ

**ቀጥተኛ ዓላማ፡-**

- ተንቀሳቃሽ ፊደላትን እንዲጠቀሙ ለማዘጋጀት
- ለንባብ ዝግጁ ያሆናሉ



*ማስታወሻ*

- ሁሉም ደረጃዎች (ተግባሮች) በሕፃናቱ መከናወን አለባቸው

*ደረጃ አንድ፡-*

- ረዳት መምህሩ ቁሶችን በመሰብሰብ ማዘጋጀት ወይም ሕፃኑ እያንዳንዱን ቁስ ቀስ በቀስ ጠረጴዛ ላይ እንዲያስቀምጥ ወይም ምንጣፍ ላይ እንዲያደርግ መርዳት
- እረዳት መምህሩ ሕፃናቱን «ምንጣፉ ላይ አንድ ዕቃ በእጄ የያዝ ይታየኛል» ይላቸዋል
- ዕቃው ማንኪያ ሊሆን ይችላል
- ያንን ማንኪያ በማንሳት በሌላ መተካት
- በዚህ ዓይነት የተለያዩ ዕቃዎችን ምንጣፉ ላይ በማስቀመጥ መቀጠል

*ደረጃ ሁለት*

- አካሄዱ ከደረጃ አንድ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን የእቃው ብዛት ግን ይጨምራል
- በመጀመሪያ ሁለት ዕቃዎችን ማስቀመጥ
- በዚህ ዓይነት በመቀጠል እንደ ልጁ ፍላጎት የዕቃውን ብዛት መጨመር
- ሕፃኑ ድምፁን በመለየት ዕቃውን ለይቶ እስኪጠቁም ወይም እስኪያነሳ ድረስ መቀጠል
- በመጀመሪያ የተለያየ ድምፅ ባላቸው እቃዎች መጀመር
- በመቀጠል ተቀራራቢ ወይም ተመሳሳይ ድምፅ ያላቸውን ዕቃዎች መጠቀም ለምሳሌ «በትንሿ አይኔ በፊደል «እ» የሚጀምር ዕቃ ይታየኛል»
- ዕቃው እርሳስ ሊሆን ይችላል

*ደረጃ ሦስት*

- እንዱን ዕቃ ካለበት ክፍል መውሰድ
  ለምሳሌ «አንድ ነገር በዚህ ክፍል ውስጥ በፊደል «አ» የሚጀምር ነገር ይታየኛል»
- ያ ነገር አትክልት ሊሆን ይችላል
- እረዳት መምህርቷ ዕቃው ያለበትን ቦታ በጣቷ ልትጠቁም ትችላለች

ለምሳሌ - «በዚህ ክፍል ውስጥ በ«መ» ጀምሮ በ«ፍ» የሚጨርስ ዕቃ ይታየኛል» ብላ እረዳት መምህርቷ ትናገራለች

- ዕቃው መጽሐፍ ሊሆን ይችላል።
- ሕፃኑ የመጀመሪያውንና የመጨረሻውን ፊደል እንዲናገር እረዳት መምህርቷ ትጋብዘዋለች

ደረጃ አራት፡-

- ቃል ስጡት ሕፃኑ ያንብበው፣ በዚህ ዓይነት ብዙ ቃላትን መስጠት
- በመጀመሪያ አጠር ያሉ ቀላትን መስጠት በጣም ጠቃሚ ነው

  ለምሳሌ - mat, car, pen, box ወዘተ

- ሕፃኑ ሲያነብ

| | |
|---|---|
| - Mat | M-a-t |
| - Box | B-o-x |
| - Pen | P-e-n |
| - Car | C-a-r |

ደረጃ አምስት፡ –

- እረዳት መምህርቷ ታነብላቸዋለች ከዚያም ሕፃናቱ የመጀመሪያውንና የመጨረሻውን ፊደል በመናገር ቃላት ይመሰርታሉ

ደረጃ ስድስት

- ሕፃኑ ራሱ ቃሉን ይናገራል ያነባልም

ዕድሜ፡ - 3½ እና በላይ

6. የአሸዋ ፊደል




ዕቃ

- 33 የመጀመሪያ ፊደል የያዘ ቀይ ሳጥን
- 33 ሁለተኛ ፊደል የያዘ ሰማያዊ ሳጥን
- 33 ሦስተኛ ፊደል የያዘ ቢጫ ሳጥን
- 33 አራተኛ ፊደል የያዘ ብርቱካናማ ሳጥን
- 33 አምስተኛ ፊደል የያየዘ አረንጓዴ ሳጥን
- 33 ስድስተኛ ፊደል የያዘ ቡናማ ሳጥን
- 33 ሰባተኛ ፊደል የያዘ ሮዝ ሳጥን

አቀራረብ

- ህፃን በመጥራት የምንሰራውን መንገር
- ወደ እቃው በመሀድ እያያዙን ማሳየት
- እቃዉን ወደ ጠረጴዛ እንዲያመጣ መንገር
- ድህረ የመዳሰስ ስሜት እንዲኖረው ለብ ባለ ውሃ ጣቶቹን ነክሮ በሮጣ ማድረቅ
- ህፃኑን እንዲያደርግ መጋበዝ
- ከአየሁሽ ጨዋታ ጋር በማዛመድ አንድ ቃል መጠየቅ

ለምሳለ. ለሴን በምን ድምፅ ይጀምራል

- ከሳጥን ውስጥ አንድ ፊደል ወይም "ለ" ማዉጣት

- ዳስሶ ህፃኑን እንዲዳስስ መጋበዝ
- በድምፅ እና በቅርፅ የተለያዩ ሦስት ፊደላትን ሦስት የማስተማሪያ ዘዴን በመጠቀም ማስተማር
- የህፃኑን ፍላጎት በመጠየቅ ሁሉንም በዚህ ሁኔታ መቀጠል

መልመጃ አንድ
- ህፃኑ ያየውን በራሱ ይሰራል

መልመጃ ሁለት
- ህፃኑን በመጥራት ሰሌን እንዲያነጥፍ በማድረግ ወደ እቃዉ ሄዶ ስሙን በታውንና አያያዙን ማሣየት
- ሰባቱንም ሳጥኖች ወደ ሰሌን ወስዶ ማስቀመጥ /መደርደር/
- ጣቶቹን በውሀ በመንከር በፎጣ አድርቆ ህፃኑን እንዲደርቅ መጋበዝ
- የመጀመሪያውን ፊደል እንደተማረ በማስታወስ ከመጀመሪያ ሳጥን አንድ ፊደል እንዲያመጣ እና ፊደሉን በስሙ ጠርቶ እንዲዳስስ መንገር
- ያወጣውን ፊደል ቤተሰብ ከሰባቱ ሳጥን እንዲያመጣ መጠየቅ

ለምሳሌ. ከሰ እስከ ሶ
- ያወጣቸውን ፊደሎች ከህፃኑ ጋር ማለት
- የማያውቀው ካለ ሦስት የማስተማሪያ መንገድ/ዘዴ በመጠቀም ማስተማር
- የልጁን ፍላጎት በመጠየቅ ከፈለገ የሚቀጥለው ጊዜ ለማስተማር እቃውን ወደ ቦታው መመለስ

መልመጃ ሦስት
- ከአሸዋ ፊደል ሳጥን ቀለም የተቀለመ ወረቀት አምጥቶ በሰሌን ጫፍ ላይ አግድም መዘርጋት

ለምሳሌ መ
- ህፃኑ አምጥቶ ስሙን እንዲለራ እንዲደስስ በቀለሙ መሰረት እንዲያስቀምጥ መንገር
- በዚህ ሁኔታ እያንዳንዱን ሣጥን እያመጣ በቀለሙ መሰረት ይደረድራል
- ከዛ በኋላ ያነባል

ቀጥተኛ አላማ
- የፊደላትን ቅርፅ ለይቶ በትክክል እንዲያየው

ተዘዋዋሪ አላማ
- ህፃኑን ለፅሁፍ ያዘጋጀዋል


የሚያስደስተው
- ሁሉንም በሚሰራበት ጊዜ

ስህተትን መቆጣጠሪያ
- በፊደላት ላይ ያለ ነጥቦች

ቋንቋ
- ፊደላት በአጠቃላይ

ዕድሜ
- ከ3½ ዓመት ጀምሮ

## ፯. በአሸዋ የተፃፈ ትንሹ የእንግሊዝኛ ፊደል



*መርጃ መሳሪያ፡-*

- ከፍ ያሉ በአሸዋ የተፃፉ ፊደላት
- አናባቢዎቹ የሚፃፉት ሰማያዊ ቦታ ላይ ነው
- ተነባቢዎች ደግሞ ሐምራዊ ቦታ ላይ ይፃፋሉ
- የድርብ ድምጽ ያላቸው ደግሞ የሚፃፉት አረንጓዴ ቦታ ላይ ነው፡፡

**ቀጥተኛ ዓላማ**

- ለሕፃኑ በማሳየትና ፍላጎቱን በማነቃቃት ለስህፈት ማዘጋጀት

**አቀራረብ**

- በአሸዋ የተፃፉትን ፊደላት ከካሳጥኑ እንዲያመጣ መንገር
- በጣት ዳሰሶ ማሳየት
- ሕፃኑም ተመሳሳይ ድርጊት እንዲፈፅም መርዳት
- ከድምፅ ጨዋታ ጋር ለመያያዝ ሕፃኑ የአንድን ቃል ድምፅ እንዲጠራ ማድረግ

ለምሳሌ፡- ሕፃኑ "mat" የሚለውን ቃል ማወቁን መጠየቅ ከዚያ በምን ድምፅ እንደሚጀምር መጠየቅ

- ሦስት በድምፅ ተቀራራቢ የሆኑትን ፊደላት ምረጡና አጠዳድሩ
- የፊደላትን ድምፅ ለሦስት ክ/ጊዜያት ያህል በዚህ ዓይነት አስተምሩ
- አንድን ፊደል ሕፃናቱ ፊት የተቀሩትን ሁለቱን ደግሞ በአንድ በኩል አስቀምጡ
- ግራ እጃችሁን ፊደሉ የተፃፈበት ቦታ ላይ ዘርጉት
- በቀኝ እጃችሁ ሁለት ጣቶች ተጫኑአቸው
- ፊደሉን እንደያዛችሁ ሦስት ወይም አራት ጊዜ ተናገሩት
- ሕፃኑም በተራው እንዲፈፅም እርዱት

- ሕፃኑን «ፊደል «ጠ»ን ልታሳየኝ ትችላለህን?» በሉት ከዚያም «አመሰግናለሁ ጠቁመኝ» ትሉታላችሁ
- ሁል ጊዜ በእጁ የጠቆመውን ፊደል ያሳያችኋል ወይም ይነግራችኋል
- ሕፃኑም መልሶ መላልሶ በድምፅ እንዲለው ጠይቁት
- ሕፃኑ በድምፅ ካለው በኋላ እንዲዳስሰው እርዱት

*መልመጃ 1*

- ጥቂት ሕፃናት በሕብረት ይቀመጣሉ
- እረዳት መምህርቷ አንዳንድ ፊደል በማንሳት ሕፃናቱ እንዲናገሩ ታደርጋለች
- ሕፃኑ ያወቀውን ፊደል ወደ ጎን ማስቀመጥ
- እያንዳንዱ ሕፃን ያወቀውን ፊደል በማንሳት ቅርፁን በጣቱ እንዲዳስስ ማድረግ
- ሕፃኑ ያላወቃቸው ፊደላት ለብቻቸው ተቀምጠው በሌላ ጊዜ እንዲቀርቡለት ይደረጋል፡፡

## ስህተትን መቆጣጠር

- ነጥብና የቁሱ ቅርፅ


**ዕድሜ:** - 4½ አመትና ከዚያ በላይ

## በአሸዋ የተሻፉ ፊደሎች-(ድምፆች)

| | | | |
|---|---|---|---|
| a | as in apple | n | as in nose |
| b | as in bed | o | as in orange /ox |
| c | as in cat | p | as in pot |
| d | as in dog | q | as in queen |
| e | as in egg | r | as in red /run |
| f | as in farm | s | as in snake |
| g | as in go /get | t | as in tap /top |
| h | as in hat | u | as in under or up |
| i | as in ink | v | as in vase /velvet |
| j | as in Jain | w | as in wall /wash |
| k | as in Kangaroo | x | as inbox |
| l | lemon | y | as in Yellow /yes |
| m | as in mat | z | as in zoo |

## 8. ድርብ ድምፅ ያላቸው (phonograms)


| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ee | Seen | Been | Week | Feed |
| 2. | or | Lord | Sport | Corn | Port |
| 3. | au | Pause | Cause | Maul | Haul |
| 4. | ie | Die | Tie | Dried | Tried |
| 5. | ai | Mail | Nail | Aim | Brain |
| 6. | oo | Moon | Roof | Spoon | book |
| 7. | ar | Car | Farm | Start | Smart |
| 8. | ou | Out | Tough | Tourch | Shout |
| 9. | ue | Blue | Glue | True | Flue |
| 10. | oa | Boat | Road | Roast | Board |
| 11. | er | Letter | Butter | Winter | Greater |
| 12. | th | Tniks | Think | Thin | Thumb |
| 13. | qu | Queen | Question | Quick | Quality |



| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 14. | sh | Fish | Shower | Shout | She |
| 15. | oy | Boy | Joy | Toy | Enjoy |
| 16. | ch | Chop | Chair | Church | Chat |

## ፱. ቅርፅ ያስቸው ስብስብ

*መርጃ መሳሪያ፡ -*



- 10 የጂኦሜትሪ ቅርፆች
- 3 የተለያዩ ቀለሞች ያላቸው እርሳሶች (ከለሮች)
- አንድ ሳጥን እኩል መጠን እንደ ፍሬም የሚያገለግሉ ወረቀቶችን የያዘ
- የጂኦሜትሪ ቅርፅ ስሞች

<u>ምሳሌ</u>

| | |
|---|---|
| ክብ | ሞላላ |
| ካሬ | ትራፕዝየም |
| ሦስት ጎናሞ | አምስት ጎንዮሽ |
| ኤሊፕስ | ስምንት ጎን |
| ሥድስት ጎን | ሬክታንግል |

**ቀጥተኛ ዓላማ፡-**

- በሰሐፍ ሕፃኑ ብቁ እንዲሆን ለመርዳት
- የመንካት ደረጃውን ከፍ ለማድረግ
- እጅን የመቆጣጠር ብቃቱን ለማዳበር

**አቀራረብ፡-**

- ሕፃኑን ወደ መደርደሪያው በመውሰድ አስፈላጊ ቁሶችን ማሳየት
- ከቁሱ ጋር ወደ መቀመጫው መመለስ
- ወረቀቱን በትክክል ስሌዳው ላይ መለጠፍ
- ፍሬሙን ላዩ ላይ ማስቀመጥ
- ባለ ቀለም እርሳሱን መምረጥ
    - የፍሬሙን የውስጠኛውን ክፍል በተመሳሳይ ፍጥነት በመጫን ይሳሉበት
    - ፍሬሙን አንስና ወረጴዛው ላይ በጥንቃቄ አስቀምጡት
    - ተጨማሪውን ነገር በተሳለው ስዕል ውስጥ መጨመር
    - የተጨመረውን ነገር በግራ እጅ አውራ ጣት በመጫን መያዝ
    - የተለያየ ቀለም ያላቸውን እርሳሶች ምረጡ
    - በቅርፁ ዙሪያ እርሳሱን ሳታነሱ በተመሳሳይ ፍጥነትነት በመጫን ቀቡ
    - ባለቀለም እርሳሳችሁን በመጠቀም፣ ቅርፁን ወደ ታች ቀቡት። ስትቀቡት ከስዕሉ መውጣት የለባችሁም።
    - ከመስመሩ አትውጡ
    - የልጆቹን ሀሳብ ወደ ስዕሉ ሳቡት
    - በተመሳሳይ ሂደት ይከናወን

- ሕፃኑ ወደ ላይና ወደ ታች ሊጠቀም ይችላል።

*መልመጃ አንድ፡-*

- ሕፃኑ እንደ አቀራረቡ ያከናውናል
- ቀስ እያለ ወይም በድንገት ሕፃኑ መስመሮችን አቀራርቦ ሊስል ይችላል።

*መልመጃ ሀ፡-*

- ሕፃኑ በቅደም ተከተል ሊሰራ ይችላል

*መልመጃ ለ፡-*

- ሁለት ተጨማሪ ነገሮችን በመጠቀም ፓተርን መስራት

*መልመጃ ሐ፡-*

- ሕፃኑ ትልቅ ወረቀት በመጠቀም ምስል ይሠራል

**ስሕተትን መቆጣጠር፡ -**

- የትርፖቹን ቅደም ተከተል እንደ መቆጣጠሪያ ይጠቀማሉ

**ዕድሜ፡ -**

- በግል ብቃት ላይ ይመሰረታል
- 4½ እና ከዚያ በላይ

**ማስታወሻ፡ -**

- ጥሩ ወረቀትና ባለ ቀለም እርሳስ (ከለር) በጣም ጥሩ ናቸው።

## 10. አማርኛ ተንቀሳቃሽ ፊደላት

- ከሀ እስከ ፐ የያዘ ቀይ ሳጥን
- ከሁ እስከ ፑ የያዘ የያዘ ሰማያዊ ሳጥን
- ከሂ እስከ ፒ የያዘ የያዘ ቢጫ ሳጥን
- ከሃ እስከ ፓ የያዘ የያዘ ብርቱካናማ ሳጥን
- ከሄ እስከ ፔ የያዘ አረንጓዴ ሳጥን
- ከህ እስከ ፕ የያዘ ቡናማ ሳጥን
- ከሆ እስከ ፖ የያዘ ሮዝ ሳጥን



አቀራረብ

- ህፃን በመጥራት ምንጣፍ እንዲያመጣ መጠየቅ
- ሰባቱንም ሳጥች አንድ በአንድ ወደ ምንጣፉ ወስዶ መደርደር
- ከሰባቱ ውስጥ ያሉትን ተንቀሳቃሽ ፊደላት ህፃኑ እንዲያሳይ እና እንዲያነብ መጠየቅ
- ህፃኑ ሁሉንም ካነበበ በኋላ ልክ እንደ ቅደም ተከተል ቃላት ማሰራት

መልመጃ አንድ

➢ ህፃኑ በአቀራረብ ያየውን ይሰራል

መልመጃ ሁለት

➢ ሀረግና አረፍተ ነገር እንዲሰራ መጠየቅ

ቀጥተኛ አላማ

➢ የቃላት አመሰራረትን ማሳወቅ

ተዘዋዋሪ አላማ

➢ ሀሳብን የመግለፅ ችሎታ እንዲኖር ያደርጋል

የሚያስደስተው

➢ ፊደላትን ለማግኘት ወዲህና ወዲያ መንቀሳቀስ

ስህተትን በቁጣጠሪያ

➢ የፊደላት አቀማመጥ

ዕድሜ

➢ ከ4 እስከ 5½ ዓመት

ማሳሰቢያ

ህፃኑ ስራውን መልሶ እንዲያነብ አይጠየቅም/አይገደድም

## 11. ተንቀሳቃሽ ፊደላት




__መርጃ መሳሪያ፡-__

- ሦስት የተለያዩ ተንቀሳቃሽ ፊደላት ስብስብ
- ሁለት ሳጥኖች የተለያየ መጠን ያላቸውን ፊደላት የያዙ
- አንዱ ሳጥን ትንሾቹን የእንግሊዝኛ ፊደል ባለአንድ ቀለም የያዘ
- እያንዳንዱ ክፍል ከ 9 - 10 የፊደል ምልክቶች ይይዛል
- አንዱ ፊደል በክፍሉ መጨረሻ ላይ ለመቆጣጠሪያነት እንዲያገለግል ማጣበቅ
- ትልቅ የመሬት ምንጣፍ

__ቀጥተኛ ዓላማ__

➢ የሕፃኑን የመመራመርና የቋንቋ ብቃት ለማዳበር

➢ ሕፃኑን ለፅሑፍ ስራ ማዘጋጀት

አቀራረብ፡-

➢ ሳጥኑን ምንጣፉ ላይ ማምጣት

➢ ለሕፃኑ አዲስ ያልሆነ አጭር የንባብ ቃላት ማቅረብ

ለምሳሌ፡ mat, pen, hat, bin, run, and hop.

- ሌላ ከሳጥኑ ውስጥ ከማውጣታችሁ በፊት ቃሉን በድምፅ አብሮ ማለት

- ከዚያ ፊደሉን ከሳጥኑ ማውጣትና በማስተካከል ምንጣፍ ላይ ማስቀመጥ
- ብዙ ቃላት መፃፍ ይቻላል::
- ድርብ ድምፅ ያላቸውን ከማስተዋወቃችሁ በፊት፣ ሕፃናቱ በነጠላ ድምፅ ብዙ መለማመድ አለባቸው
- ሕፃናቱ እንቅስቃሴ ከተለማመዱ በኋላ በራሳቸው ሊቀጥሉ ይችላሉ::
- እያንዳንዱ ሕፃን የፃፈውን እንደገና እንዲያነብ ወይም ፊደሉን በትክክል እንዲናገር አይገደድም::

<u>**መልመጃ አንድ:-**</u>

- ሕፃኑ እንደ አቀራረቡ ያከናውናል

<u>**መልመጃ ሁለት:-**</u>

- ሕፃኑ ወደ ሰሀፊት በማደግ pink, box, blue, pen መዘተ በተንቀሳቃሽ ፊደል መፃፍ
- በመቀጠል ሕፃናቱ አረፍተ ነገሮችንና ታሪኮችን መናገር ይጀምራሉ


**ዕድሜ:-**

- 5 አመትና ከዚያ በላይ

## 12. በስሸዋ የተፃፉ ትልቁ የእንግሊዝኛ ፊደላት:-

<u>**መርጃ መሳሪያ**</u>

- ሁለት ሳጥኖች በአሸዋ የተፃፉ ፊደላትን የያዘ፣ አንዱ ሳጥን ትንሹን ፊደል የያዘ
- ሌላ በአሸዋ የተፃፉ ትልቁን የእንግሊዝኛ ፊደላትን የያዘ
- ካርዶች፣ ትልቁና ትንሹን የእንግሊዝኛ ፊደሎች ጎን ለጎን የያዙ
- ትልቁና ትንሹ የእንግሊዝኛ ፊደሎች በተለያዩ ወረቀቶች ላይ የተፃፉ
- በጣት በመንካት ስሜት የሚሰጡ ቁሶች




<u>**አቀራረብ**</u>

- በጣት መንካት
- ሦስት የሚመሳሰሉ ፊደሎችን በአሸዋ ከተፃፉት ከትልቁ የእንግሊዝኛ ፊደል ውስጥ ምረጡ
- ሕፃናቱ ደግሞ ትንሹን የእንግሊዝኛ ፊደል ተመሳሳዩን ይምረጡ
- ሕፃናቱ በጣታቸው በመጫን ትንሹን የእንግሊዝኛ ፊደል ያንብቡት
- ለሕፃናቱ እንዴት አድርገው ትልቁን የእንግሊዝኛ ፊደል ቅርፅ፣ ምልክት እንደሚያደርጉ አሳዩአቸው
- ለሕፃናቱ ትልቁና ትንሹ የእንግሊዝኛ ፊደል ተመሳሳይ ድምፅ እንዳላቸው አስረዷቸው
- ትልቁን የእንግሊዝኛ ፊደል ልክ እንደ ትንሹ ፊደል አንብቡት
- ለሕፃናቱ ትክክለኛውን የፊደሉን ስም ንገሯቸው እናንተ የጠቆማችሁ ድምፁን ንገሯቸው ለምሳሌ ፊደሉ «ቢ» ይባላል በሏቸው:: የቀሩትንም ፊደሎች ተመሳሳይ መልክ ፊስሙ
- ትንሹንና ትልቁን ተመሳሳይ የእንግሊዝኛ ፊደሎች ጎን ለጎን አስቀምጡአቸው::

- የፊደሎችን ስም እያሳዩዋቸው ትክክለኛውን ስም ንገሯቸው
- ከትንሽ የእንግሊዝኛ ሆሄያቱን ፊደሎች ሳጥናቸው ውስጥ መልሱ
- ሆሄያቱን ትልቁን የእንግሊዝኛ ፊደሎች ትክክለኛ ስማቸውን በሦስት ክ/ጊዜያት አስተምሯቸው
- ከጊዜ ወደ ጊዜ ድምፁን ከፊደሉ ጋር አዛምዱና ንገሯቸው
- ከተቀሩትም ጋር በተመሳሳይ መልክ ቀጥሉ

**መልመጃ አንድ:-**

- መልመጃ በካርድ ሥሩ
- በመጀመሪያ ትልቁን ፊደል ቀጥሎ ትንሹን ፊደል በመውሰድ ጎን ለጎን በአንድ ትልቅ ካርድ ላይ አሳዩ
- ከሕፃናቱ ጋር ሁሉንም ካርዶች ተመልከቱ:: ሕፃናቱ ስማቸውን ከተናገሩ በኋላ ምንጣፉ ላይ ጎን ለጎን አስቀምጧቸው
- ትልቁንና ትንሹን፣ በተለያዩ ካርዶች ላይ ያሉትን፣ የእንግሊዝኛ ፊደላት ደባልቁ
- ምንጣፉ ላይ ከደባለቁት ውስጥ ተመሳሳዩን ፊደላት ለይታችሁ አዛምዱ

*መልመጃ ሁለት*

- ሕፃናቱ ትልቁን ፊደል ምንጣፉ ላይ ያስቀምጣሉ
- ሕፃናቱ ሁሉንም ትናንሽ ፊደላት በአንድ ላይ ምንጣፉ ላይ ይደባልቁታል
- ከዚያ ሕፃናቱ እያንዳንዱን ትንሽ ፊደል ከተመሳሳይ ትልቅ የእንግሊዝኛ ፊደል ጋር ያዛምዱታል ሲያዛምዱ ትንሹን ከትልቁ በቀኝ በኩል ያስቀምጣሉ::
- በመጨረሻው ሕፃናቱ መቆጣጠሪያ ካርዱን ያዩታል::

*መልመጃ ሦስት*

- ሁለት ምንጣፎችን አራርቃችሁ አንጥፉ
- ሁሉን ትላልቅ ፊደሎች ደባልቁት
- በሌላኛው ምንጣፍ ትናንሽ ፊደላትን ደባልቁ
- ሕጻናቱ አንድ ትልቅ የእንግሊዝኛ ፊደል ከመረጡ በኋላ ወደ ሁለተኛው ምንጣፍ በመሄድ ተመሳሳዩን ትንሹን ፊደል ይመርጣሉ
- ከዚያ ሕፃናቱ ሁለቱን ያዛምዳሉ
- ሕፃናቱ ትንሹን ፊደል ምንጣፉ ላይ ይመልሱታል ወይም እንደተዛመደ ያስቀምጡታል
- ሕፃናቱ በዚህ አይነት መንገድ ሁሉንም ፊደሎች ያዛምዳሉ
- ከ "A - Z" ያለውን የእንግግዝኛ ፊደል ቅደም ተከተሉን በ "a,b,c..." ዝማሬ ድምፅ አስተምሩአቸው

ዕድሜ:-

- 4 አመትና ከዚያ በላይ

## 13. በአሸዋ የተሰሩ ፊደላትን መዳሰስና መፃፍ

መርጃ መሳሪያ፡-

- ትሪ ፤ ስፖንጅ ለብ ካለ ውሃ ጋር፤ ወረቀቶች፤ መወልወያ ጨርቅ፤ የጥቁር ሰሌዳና ቾክ ማጥፊያ (ዳስተር)





ቀጥተኛ ዓላማ፡-

- ሕፃኑን ፊደል መፃፍ ማለማመድና ክህሎቱን ለማዳበር

አቀራረብ

- ሕፃኑ በጣቱ እንዲዳስስ መጋበዝ
- ቁሶቹ ከዚህ በሚከተለው ቅደም ተከተል ይቀመጣሉ፡- በግራ በኩል ስፖንጅ እና ውሃን የያዘ ትሪ፤ በቀኝ በኩል ደግሞ ጠመኔና ጥቁር ሰሌዳ ይሆናሉ::
- ቾክ ማጥፊያው ከጥቁር ሰሌዳው በላይ ይቀመጣል
- በአሸዋ የተፃፈውን ፊደል አንሱ
- ቅርጽ ማስያዣያውን በመውሰድ ጥቁር ሰሌዳ ላይ በጠመኔ ፃፉ
- ዘወትር ፊደሉቹ ከተፃፉ በኋላ በጣታችሁ ዳስሱ
- አድርቁትና ሁለተኛውን የፊደል ቅርፅ ፃፉ
- በዳሰሳ ፊደሉን ካወቃችሁ ፊደሉን ተናገሩት ከዚያም ጥቁር ሰሌዳ ላይ ፃፉት::
- ጠመኔ ከተጠቀማችሁ በኋላ እጃችሁን በረጠበ ስፖንጅ ላይ ጥረጉት:: ይህ ደግሞ በአሸዋ የተፃፈውን ንፁህ ያደርገዋል::
- ጥቂት ፊደሎቹን ከፃፉችሁ በኋላ ሕፃናቱ እንዲፅፉ ጋብዙአቸው
- ሰሌዳውን በፅሕፈት እንዲሞሉ ሕፃናቱን እርዱአቸው
- ሕፃናቱ በትክክል መገልበጣቸውን እርግጠኛ ሁኑ

መልመጃ አንድ

- ሕፃኑ በአሸዋ ፊደል መልሶ መሳልሶ መስራቱን ይቀጥላል

መልመጃ ሁለት፡ -

- ሕፃኑ በጣቱ ይዳስሳል
- ሕፃኑ በአሸዋ ከተሰራው ፊደል በልሙጥ ወረቀት መገልበጥ
- በየጊዜው ሕፃኑ በአሸዋ ከተፃፈው ፊደል እንዲገለብጥ ያስፈልጋል

መልመጃ ሦስት፡-

- ሕፃኑ መስመር ባለው ሰሌዳ ላይ ይፅፋል

- ሕፃኑ ተመሳሳይ ሂደት በመከተል በጣቱ ከነካካ በኋላ ቁሉን በሥን-ሥርዓት ያስቀምጣል።

**መልመጃ አራት**

- ሕፃኑ መስመር ባለው ወረቀት ላይ ከላይ በተጠቀሰው መንገድ ይሰራል

**ዕድሜ፡-**

- 4½ አመትና ከዚያ በላይ

## 14. በአሸዋ የተፃፉ ፊደላትን ከዳሰሰ በኋላ በየአይነታቸው ማስቀመጥ




**መርጃ መሳሪያ፡-**

- ጥቁር ሰሌዳ፣ ጠመኔ፣ በአሸዋ የተፃፉ ፊደሎችን የያዘ ሳጥን፣ ልሙጥ ወረቀት፣ እርሳስ

**ቀጥተኛ ዓላማ፡-**

- በአሸዋ በተፃፉ ፊደላት በመጠቀም የሕፃኑን የማወቅ ፍላጎት ለማዳበር

**አቀራረብ፡-**

- በጣት በመነካካት አንዱን ፊደል ማውጣት
- ፊደሉን ገልብጡና ለሕፃናቱም ተመሳሳይ ፊደል መስራት እንደሚቻል ንገሩአቸው
- ለምሳሌ "c" ከፃፋችሁ በኋላ በጣታችሁ ዳስሱት ከዚያ ሁሉንም ፊደሎች ተራ በተራ ከፃፋችሁ በኋላ ተመሳሳይ የሆነውን በአንድ በኩል አስቀምጡት

  ለምሳሌ c, a, o, d, g, q, e የመሳሰሉት መስርተው ከሆነ ከ "c" ጋር የመመሳሰል ፀባይ አላቸው

- ከ"c" ጋር የሚመሳሰል ቅርፅ የሌላቸውን በሌላኛው የምንጣፍ ጎን አስቀምጡ።
- ተመሳሳይ ቤተሰብ ያላቸውን ፊደሎች ካገኛችሁ በረድፍ አስቀምጡና ሕፃናቱ ይገልብጡ።

*መልመጃ አንድ*

- ሕፃናቱ ተመሳሳይ ቤተሰብ ያላቸውን ፊደሎች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ወይም በልሙጥ ወረቀት ላይ ይፃፏቸው

**ዕድሜ**


- 5 አመትና ከዛ በላይ

## 15. ፊደላትን በመስመር ማስቀመጥ

**መርጃ መሳሪያ:**

- ሁለት የተለያዩ ቀለሞች አግድሞሽ የተጠለፈባቸው (ሰማያዊና ቀይ) የተዘረጉ ምንጣፎች





- ትንሹን የእንግሊዝኛ ፊደል (a - z) የያዘ ሳጥን

**ቀጥተኛ ዓላማ**

- ሕፃናትን ፊደሎች ያላቸውን ቦታ በማሳየት ዕውቀታቸውን ማስፋት

**አቀራረብ**

- ምንጣፉን ዘርጉት
- ፊደሎቹን አውጡና ያለ ምርጫ ምንጣፉ ላይ መዘርጋት
- የትኛው ፊደል በሁለቱ ሰማያዊ መስመሮች ውስጥ እንደሚገባ አረጋግጡ
- በትክክል የሚገቡትን ፊደሎች ከለያችሁ በኋላ ሌሎቹ የት እንደሚገቡ ፈልጉ

**መልመጃ 1**

- የሚሠራው ራሱ ሲሆን የምናሰራው ፊደሎቹን ምንጣፍ ላይ በመዘርገፍ ነው

**መልመጃ ሀ:-**

- ሕፃኑ ፊደሎቹን መስመር ባለው ሰሌዳ ላይ ይገለብጣል

**መልመጃ ለ:-**

- ሕፃኑ ፊደሉን መስመር ባለው ወረቀት ላይ ይፅፋል

**ዕድሜ:-**

- 5½ አመትና ከዛ በላይ


## 16. በመስመር ወረቀት የተፃፈ

**መርጃ መሳሪያ**

- በመያዥያ የተቀመጡ በብዛት የተፃፉ ወረቀቶች
- ደማቅ መስመር ወረቀትና እርሳስ

**ቀጥተኛ ዓላማ**

- ሕፃኑ በዕሕፈት ጥሩ ደረጃ እንዲኖረው ለመርዳት




**አቀራረብ**

- በህፃኑ ስም ጀምሩ
- እንዴት እንደሚፃፍ አሳዩት
- የሚፃፉትን በቅደም ተከተል አስቀምጡ
- በመስመሮቹ መካከል ሰፊ ቦታ ይኑረው
- አጭር የሚገለበጡ አንድ ወይም ሁለት አረፍተ ነገሮች ይኖሩታል
- ሦስተኛው ግልባጭ የሚገለበጡ ጥቂት ስሞች፤ አረፍተ ነገሮችን ይይዛል
- ሕፃኑ በተመሳሳይ ጠረጴዛ ላይ ግልባጩ ይኖረዋል
- ሕፃኑ ግልባጩን ይወቅና መስመር ባለው ወረቀት ይፃፍ

ዕድሜ:-

5½ ዓመትና ከዛ በላይ

## 17. የሥእል ማስቀመጫ ፍሬም

መርጃ መሳሪያ:-


- ሁለት የተለያዩ ባለ መስመር ወረቀቶችና እርሳስ

ቀጥተኛ ዓላማ:-

- በጣም ውብ የሆኑ ፅሑፎችን እንዲፅፉ ለመርዳት

አቀራረብ:-

- እንዴት አድርገው በባለ መስመር ወረቀት ፍሬሙን እንደሚስሉ አሳዩዋቸው
- ሕፃናቱ በፍሬሙ ውስጥ አንዳንድ መስመሮችን እንዲፅፉ እርዱአቸው
- የፍሬሙን ጠርዝ እንዴት እንደሚያስውቡ አሳዩዋቸው




ዕድሜ:-

- 5½ ዓመት እና ከዛ በላይ

## 18. የዕቃ ሳጥን

መርጃ መሳሪያ:-


- ሳጥኑ 12 እቃዎችን ይይዛል::
- የእቃው ስም የተፃፈበት ፊደል ከአሸዋው ፊደል ጋር መመሳሰል ሲኖርበት ሕፃናቱም ድምፁን

  የተማሩት መሆን አለበት::

- ትንሹ ሳጥን የእቃዎቹ ስሞች የተፃፉበትን ካርዶች ይይዛል ::
- ወረቀት፣ እርሳስና መቀስ


ቀጥተኛ ዓላማ:-

- ሕፃኑ የተፃፉት ቃላት የድምፆች ሕብረት መሆናቸውን
- ቃላቱ በምልክት የሚወከሉና ትርጉም ያላቸው መሆናቸውን እንዲያውቅ መርዳት



## አቀራረብ

- ሕፃኑ ከሳጥኑ ውስጥ ዕቃዎቹን አውጥቶ ምንጣፍ ላይ እንዲያስቀምጥ መጋበዝ
- ሕፃኑ እቃውን እያወጣ 'ሳለ ስሙንም መናገር ይኖርበታል ለምሳሌ ባርኔጣ፣ መኪና፣ ድመት ወዘተ.
- «ምን ዕቃ እንደማስብ ታውቃለህ» ብላችሁ ሕፃኑን ጠይቁት
- ሕፃኑ በእጁ አንድ ዕቃ ይጠቁማል




- ሕፃኑም የጠቆመው ዕቃ እናንተ ያሰባችሁት እንዳልሆነ ንገሩት
- ሕፃኑም የተፃፈውን ካርድ እንዲያነብ እርዱት
- ካርዱን የሚወክለው እቃ ላይ ያስቀምጥ
- ለምሳሌ ካርዱ የሚለው «በአሸዋ የተፃፈ ፊደል» ከሆነ ወስዳችሁ በአሸዋ የተፃፈው ፊደል ላይ አስቀምጡት
- ሕፃኑ መጫወት የሚፈልገውን ያህል መልሶ መላልሶ ዕቃው ላይ ያለውን ያንብብ፡፡
- በመጨረሻ ልጁ ካርዶቹን ሰብስቦ ቦታቸው እንዲያስቀምጥ እርዱት

## ኢ-ቀጥተኛ ዓላማ

- የአእምሮ እንቅስቃሴ ወይም ልምምድ ለማዳበር

## ስሕተትን መቆጣጠር

- የሕፃኑን የማንበብ ችሎታ

## ዕድሜ፡-

- 5½ እና ከዛ በላይ